## በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደ በጉለሌ ክ/ከተማ ት/ጽ/ቤት

## የ6ኛ ክፍል የአንደኛ ወሰነ ትምህርት የአማርኛ ትምህርት ሞዴል ፈተና ጥር 2018 ዓ.ም

**የጥያቄ ብዛት:** 40 **የተፈቀደዉ ሠዓት፡-** 1 ሠዓት

ይህ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ነዉ ። በዚህ ፈተና ውስጥ 40 ጥያቄዎች ተካተዋል ። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ የሆነዉን አማራጭ የያዘውን ፊደል በመምረጥ ለመልስ መስጫ በተሰጠዉ ወረቀት ላይ በማጥቆር መልስ ይሰጣል። እያንዳንዱን ትዕዛዞች በጥንቃቄ በማንበብ ፈተናውን መስራት ይጠበቅባችኋል። ፈተናዉን ሠርቶ ለመጨረስ የተፈቀደው 1 ሠዓት ነው ።

በፈተናው ወቅት ሲኮርጅ ወይም ሲያስኮርጅ የተገኘ ተማሪ ፈተናው አይያዝለትም፣ ፈተናውን እንዳይፈተንም ይደረጋል ።

ፈተናውን መስራት ከመጀመራችሁ በፊት በመልስ መስጫው ወረቀት ላይ መሞላት የሚገባቸውን መረጃዎች ሁሉ በጥንቃቄ መሙላት አለባችሁ።

***ፈተናውን መስራት ጀምሩ ሳይባል መጀመር አይፈቀድም***

LIVEWORKSHEETS

**መመሪያ አንድ:- የሚከተሉትን ጥያቄዎች በትክክል በማንበብ ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ።**

1. እኩይ ለሚለው ቃል ተመሳሳይ ፍቺ የሆነዉ ቃል የቱነዉ?

   ሀ) መጥፎ ለ/ ሰናይ ሐ/ መልካም መ/ ጥሩ

2. **ተዘባነነ** ለሚለዉ ቃል ተቃራኒ ፍቺ ሲሆን የሚችለዉ ቃል የቱ ነዉ?

   ሀ) ተጀነነ ለ/ ተኩራራ ሐ/ ተስማመጠ መ/ ተሰጠጠ

3. አንድን ጸሑፍ ከመፃፋችን በፊት ቅደም ተከተላዊ ሂደቱን ቀድመን የምንነድፍበት ሂደት ምን ይባላል?

   ሀ/ ዘገባ ለ/ ቢጋር ሐ/ ማስታወሻ መ/ መመሪያ

4. ሰናይት <u>**ወርቅ**</u> ገዛች። የተሰመረበት ቃል __________ ነዉ።

   ሀ/ ባለቤት ለ/ ግሰ ሐ/ ተሳቢ መ/ ተወሳጠ ስም

5. <u>**በየታዛዉ**</u> ተጠልለው የነበሩት ሰዎች ተበተኑ። የተሰመረበት ቃል ትርጉም____________ ነዉ።

   ሀ) መጠለያ ለ/ ምግብ ቤት ሐ/ ሻይ ቤት መ/ መኝታ ቤት

6. አቶ አለሙ ፈረስ ጠፍቶበት <u>**ሲዋትት**</u> ዋለ። የተሰመረበት ቃል አቻ ትርጉም የሚሆነው የቱ ነዉ?

   ሀ/ ሲያስቅስ ለ/ ሲፈራ ሐ/ ሲባክን መ/ ሲርበተበት

7. ምዕላድ በስንት ይከፈላል? ሀ/ በአንድ ለ/ በሁለት ሐ/ በሶስት መ/ በአራት

8. ብቻውን መቆም የሚችል ትርጉም ያለዉ ቃል____________ ይባላል ?

   ሀ/ ነፃ ምዕላድ ለ/ ጥገኛ ምዕላድ ሐ/ ተወሳከ ግስ መ/ ተወሳጠ ስም

9. ህፃኑ ልጅ በለጋ እድሜዉ <u>**ተቀጠፈ**</u>። የተሰመረበት ቃል አዉዳዊ ፍቺ ምንድነዉ?

   ሀ/ ተቆረጠ ለ/ ሞተ ሐ/ ታመመ መ/ ተቀነጠሰ

10. አባቴ ከስራ በመቀነሱ <u>ቀዘመ</u>። የትሰመረበት ቃል አዉዳዊ ፍቺ ምንድነዉ?

    ሀ/ አሽካካ ለ/ ተደሰተ ሐ/ ተከዘ መ/ ፈነጠዘ

11. አንድን ሁነት በጊዜ ቅደም ተከተል የሚያቀርብልን የድርሰት አፃፃፍ ዓይነት___________ ነዉ?

    ሀ/ አመዛዛኝ ለ/ተራኪ ሐ/ ገላጭ መ/ አወዳዳሪ

12. ልጁ <u>ከፉኛ</u> ታሟል። በዓረፍተ ነገሩ ውስጥ የተሰመረዉ ቃል______________ነው።

    ሀ/ ስም ለ/ ቅፅል ሐ/ ግስ መ/ ተዉሳከ ግስ

LIVEWORKSHEETS

13. በአንቀፅ ዉስጥ የጽሑፉን አጠቃላይ ሃሳብ የሚይዘዉ ዓረፍተ ነገር ምን ይባላል?

ሀ/ መዘርዝር ዓረፍተ ነገር ለ/ ሃይለ ቃል ሐ/ ድርሰት መ/ አስተዋጽኦ

14 ከልቦለድ አሳባዊን መካከል በልቦለድ ውስጥ ማስተላለፍ የተፈለገውን ዋና ሀሳብ ወይም መልእክት

----------- ነዉ:: ሀ/ ሴራ ለ/ ጭብጥ ሐ/ መቼት መ/ ትልም

15. መሀመድ *ድንገት* መጣ ። የተሰመረበት የግስ ገላጭ ምንን ያመለክታል?

ሀ/ ሁኔታን ለ/ ቦታን ሐ/ መጠንን መ/ ጊዜን

16. ልጁ ቶሎቶሎ መጣ ። የተሰመረበት ቃል ሰዋሰዋዊ ተግባር ምንድነዉ?

ሀ/ ግስ ለ/ተወሳከ ግስ ሐ/ ተወሳጠ ስም መ/ መስተዋድድ

17. በድርሰታችን የሚለው ቃል በምዕላድ ተነጣጥሎ ሲፃፍ__________ ነዉ?

ሀ/ በድርሰታችን ለ/ በ-ድርሰት-ኣችን ሐ/ በድርሰት-ኣች-ን መ/ በ-ድርሰት-ኣች-ን

18. ዘመን-አዊ-ነት-ኣችን የሚለው ቃል ተጣምሮ ሲፃፍ ትክክለኛውን ቅርፅ የሚይዘው በየትኛው አማራጭ

ነው? ሀ/ የዘመናዊነታችን ለ/ የዘመን አዊ-አችን ሐ/ ዘመናዊነታችን መ/ የዘመናዊ

19. ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት አማራጮች ዉስጥ ነጠላ ቁጥር የሆነዉ የቱ ነዉ?

ሀ/ ሰዎች ለ/ ተማሪ መ/ ቤቶች መ/ በጎች

20. ጥጆች በሚለዉ ቃል ያለዉ ቅጥያ ምንን ያመለክታል?

ሀ/ ነጠላ ቁጥርን ለ/ ብዙ ቁጥርን ሐ/ ፆታን መ/ መደብን

**መመሪያ ሁለት:-** ከተራ ቁጥር 21-23 ያሉትን ጥያቄዎች ከዚህ በታች ያለውን ድርሰት መሰረት በማድረግ

ትክለኛውን መልስ ምረጡ

ከሙሽሮቹ ፊት መሀል ስፍራ የሴቶች የአንገትና ወገብ፣የወንዶች ትከሻና ደረት የሚለካበት መድረክ ሆነ። ባህላዊ እስክስታና ጭፈራ ቀልጧል። የሚያጨበጭበው ዜማውን የሚቀበለውና የሚያደምቀው የሚወዛወዘዉ ሁሉ ፊቱ ላይ ሞቅ ያለ የደስታ ፈገግታ ይታይበታል::

21. የዚህ አንቀጽ ደባቡ ምንድነዉ? ሀ/ የግብዣ ለ/ የጭፈራ ሐ/ የሠርግ መ/ የዳንኪራ

22. ከላይ በቀረበው ድርሰት መሰረት **ቀልጧል** የሚለዉ ቃል ትክክለኛ ትርጉም ከሚከተሉት አማራጮች መካከል የትኛው ነዉ ? ሀ/ ቀውጦታል ለ/ ፈሶበታል ሐ/ ወዝቶበታል መ/ ደምቆበታል

LIVEWORKSHEETS

23. ከስ የቀረበው አንቀጽ የተፃፈበት የድርሰት አይነት ከሚከተሉት የትኛው ነዉ?

ሀ/ ተራኪ ለ/ ገላጭ ሐ/ አመዛዛኝ መ/ ስዕላዊ

24. ተመሳሳይነት ያላቸው ነገሮች በጋራ የሚጠሩበት ስም ምን ይባላል?

ሀ/ የረቂቅ ስም ለ/ የወል ስም ሐ/የተፀዉዖ ስም መ/ተወላጠ ስም

25. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል **ረጅም** ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይ ሊሆን የሚችለው ትክክለኛ ፍቺ

የቱ ነው? ሀ/ መሰሉ ለ/ አጭር ሐ/ ምድር አብስ መ/ ጉቶ

26. **ማዳበር** ለሚለው ቃል ተመሳሳይ ፍቺ ----------------ነዉ?

ሀ/ መመሳሰል ለ/ መፃፍ ሐ/ ማበልፀግ መ/ መውሰድ

27. ከዚህ በታች ተዘበራርቀዉ የተፃፉትን ዓረፍተ ነገሮችን በመጠቀም አንቀጽ ለመጻፍ ትክክለኛ ቅደም ተከተል የሆነው የቱ ነዉ?

1/ የኤች አይ ቪ ቫይረስ በሀገራችን መስፋፋቱን ቀጥሏል።

2/ ከዚህ ባለፈም ለኢኮኖሚ ዉድቀት ያጋልጣል።

3/ ስለዚህ ቫይረሱ እንዳይሰራጭ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባናል።

4/ የቫይረሱ መስፋፋት ደግሞ የብዙ ሰዎችን ህይወት ያጠፋል።

ሀ/ 1፣4፣ 2፣3 ለ/4፣2፣31 ሐ/1፣3፣2፣1 መ/ 3፣1፣4፣2

28. **ወንበሮቻችን** የሚለዉ ቃል በትክክል ተነጣጥሎ የተፃፈው በየትኛው አማራጭ ነዉ?

ሀ/ ወንበር-ኦች-ኣችን ለ/ ወንበሮች -ኣችን ሐ/ ወንበር-ዎች-አችን መ/ ወንበር -ኦች-ች-ን

29. **ምርቃት** ለሚለው ቃል ተቃራኒ ፍቺ የሚሆነው የቱ ነዉ?

ሀ/ ስጦታ ለ/ ልገሳ ሐ/ እርግማን መ/ ልመና

30. ስለ ቃላዊ ግጥም ትክክል **ያልሆነው** የቱ ነዉ?

ሀ/ ወግና ልማዳቸውን አጠናክረው ያቀዩበታል።

ለ/ ህዝቦች ማንነታቸውን ይገልጹበታል።

ሐ/ ፍቅር ጥላቻቸውን ይገልፁበታል።

መ/ የቃላዊ ግጥም ባለቤት ግለሰብ እንጂ ማህበረሰብ አይደለም ፡፡

LIVEWORKSHEETS

31. ጥምር ቃልን ለመመስረት የምንጠቀመው ስርዓተ ነጥብ ምን በመባል ይታወቃል?

ሀ/ ንዑስ ጭረት ለ/ ዐብይ ጭረት ሐ/ ነጠላ ሰረዝ መ/ ድርብ ሰረዝ

32. አባቴ <u>አሁን</u> ይመጣል ። በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል የምን ተወሳከ ግስ ነው?

ሀ/ የጊዜ ለ/ የቦታ ሐ/ የሁኔታ መ. የስፍራ

33. **ክሳትይታ** ይህ ተዘበራርቆ የተቀመጠው ቃል ትርጉም እንዲሰጥ ተደርጎ ሲዋቀር ከተሰጡት አማራጮች መካከል የቱ ነዉ? ሀ/ ሳይትክተ ለ/ ክሳትታይ ሐ/ ሳይታክት መ/ ክትሳይታ

34. የአንድን ነገር ምንነት በአይነ ህሊናችን እንድናይ፣ በአዕምሯችን ምስል እንዲከሰት የሚያደርግ የድርሰት አይነት ምን ይባላል?

ሀ/ አመዛዛኝ ለ/ተራኪ ሐ/ ገላጭ መ/ ስዕላዊ

35. ተማሪዎቹ ጥሩ ውጤት አስመዘገቡ። የሚለው ዓረፍተ ነገር የተነገረበት የጊዜ አይነት ________ *ነው?*

ሀ/ የሃላፊ ጊዜ ለ / የአሁን ጊዜ ሐ/ የወደፊት ጊዜ መ/ ጊዜዉ አይታወቅም

36. ነኢማ ባለፈው አመት ቤተሰቦቿን ጠይቃ ተመለሰች ። በዓረፍተ ነገሩ ወሰጥ የተገለጸው ጊዜ አይነት ----------- ነው። ሀ/ የአሁን ጊዜ ለ/የሃላፊ ጊዜ ሐ/ የሁኔታ መ/ ጊዜዉ አይታወቅም

37. <u>**ጥሪት**</u> የሚለው ቃል አማራዊ ፍቺ ------------- ነዉ።

ሀ/ ሰልጣን ለ/ ልፋት ሐ/ ንብረት መ/ ሀሳብ

38. <u>**ዱባ**</u> የሚለው ቃል ፍካራዊ ፍቺ --------- ነዉ።

ሀ/ ተቀቅሎ የሚበላ ለ/ ቀጭን ሐ/ ፍሬ መ/ ወፍራም

39. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል ቅድመ ግንድ ቅጥያ በመነጣጠል የተፃፈዉ የቱ ነዉ?

ሀ. ገበሬ --ዎች ለ. እንደ-ወንድሙ ሐ. ተራራ-- ኣማ መ. ተማሪ--ዎች

40. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል ድህረ ግንድ ቅጥያዎችን አጣምሮ የያዛዉ የቱ ነዉ?

ሀ. ወደ-- መስኮት ለ. ስላ -- ጠራኝ ሐ. ሰዎች መ. እንደ--መጣች

LIVEWORKSHEETS

LIVEWORKSHEETS